## 2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር (በምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በ9ኛክፍል ተተኳሪነት

አለማየሁ ተመስገን (ዶ/ር) ፣ አለባቸው ቢያድጌ (ዶ/ር)

### አህፅሮተ ጥናት

አንድ የህንፃ ባለሙያ ንድፉን (Blue Print) ተጠቅሞ ማራኪና ቆንጆ ህንፃ እንደሚገነባ ሁሉ አንድ ፀሀፊም ቃላትን ተጠቅሞ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ ፅሁፍ መፍጠር አለበት። መሀንዲሱ የፊዚክስን ህግ መረዳት እንዳለበት ሁሉ ፀሀፊውም የቋንቋውን ህግ እና የቃላትን ባህሪ መረዳት ይኖርበታል (Cook፣ 2010፣97-106)። ከዚህ በመነሳት ለመሆኑ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር ምን ይመስላል? የሚለውን መመርመር የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ነበር። ይህን ዓላማ ለማሳካት ደግሞ በምስራቅ ጎጃም ዞን ከሚገኙ 64 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችበእጣ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። ከእነዚህ ትምህርትቤቶች ውስጥ ደግሞ ዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋየሚያስተምሩ 37 መምህራን በጥቅል የንሞና ዘዴ የተመረጡ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፅሁፍ መጠይቅና ምልከታ ናቸው። ከፅሁፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች በአሃዛዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል። ይኸውም መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ በፅሁፍ መጠይቅ አተገባበራቸውን ደግሞ በምልከታ ተሰብስቧል፤ በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በዓይነት በዓይነት ከተደራጀ በኋላ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል። ከምልከታ የተገኘውን መረጃ በተመለከተም የሁለቱ ተመልካቾች አማካይ ውጤት ተወስዶ ለትንተና ሲውልየተገኘውም መረጃ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል። ከዚያም በመምህራን የሰዋስው እርማት ግንዛቤና በአተገባበራቸው መካከል የሚኖረው ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ዘዴ ተረጋግጧል። በመጨረሻም የመጀመሪያውን ዓላማ በተመለከተ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ በአማካይ 87.95 ሲሆን ከሚጠበቀው አማካይ (111) በ 23.054 ያነሰ ነው። ይህ ውጤት ማለትም መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤበባለ ሁለት አቅጣጫ ፍተሻ ($t=22.733$, $df=36$, $p<0.05$) ጉልህ ልዩነት አሳይቷል። በመሆኑም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ

ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛና በመካከላቸውም ጉልህ የሆነ የግንዛቤ ልዩነት ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው አተገባበርም በአማካይ 73.76 ሲሆን ከሚጠበቀው አማካይ (111) ያነሰ ነው፡፡ ይህ በመምህራን መካከል ያለው የአተገባበር ልዩነትም ጉልህ ልዩነት (t=42.795,df=36, P<0.05) ያሳየ መሆኑን የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡ በመጨረሻም በመምህራን የሰዋስው እርማት ግንዛቤና አተገባበር መካከል ጠንካራ ተዛምዶ (r=0.998) እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ሲጨምር አተገባበራቸው የሚጨምር ሲሆን በተቃራኒው ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ሲቀንስ አተገባበራቸው የሚቀንስ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ውጤቶች በመነሳትም ምክረ-ሃሳቦች ተሰጥተዋል፡፡

**መፍቻ ቃላት** (Key Words): የሰዋስው እርማት፣ የሰዋስው እርማት ግንዛቤ፣ የሰዋስው እርማት አተገባበር፡-

[2] ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ የማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል፣ ስልክቁጥር 0911316521፣ E-mail: haddisalex@gmail.com

[3] ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ የማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል ስልክ ቁጥር 0939634214፣E-mail: alebekb@gmail.com

## 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች አራቱን ክሂሎች ማዳበርና ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች ማበልፀግ ነው፡፡ እነዚህ ዓላማዎች አማርኛን እንደ መጀመሪያም ሆነ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተነደፉ ቢሆንም እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ አገራዊ ተግባቦትን ለማሳለጥ እንደሚያስችል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በ1994 ዓ/ም ባሳተመውና "የማስፈፀምአቅም ግንባታ ስትራቴጂ" በሚለው ሰነድ ላይ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡ ይሁን እንጅ ከተለያዩ ክልሎች የመጡና አማርኛ ቋንቋን እንደአፍ መፍቻም ሆነ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚያጠኑ ተማሪዎችን ችሎታ ስንመለከተ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ለአብነት ባዩ

(2000) በየደረጃው እየተመረቀ የሚወጡት ተማሪዎች ተራ ዘገባ ወይም ሪፖርት ለማዘጋጀት የሚያስችል ብቃት እንደሌላቸው ይገልፃሉ፡፡

Celce-Murcia (1991፡256) ተማሪዎች የፅህፈት ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ በተደጋጋሚ ማረምና ሰዋስዋዊ ስህተቶቻቸውን በየደረጃው በመንገር እንዲያስተካክሉ ማድረግ እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡ ሰዋስው በቋንቋ ማስተማር ውስጥ ለብዙ ሺህ ዓመታት ያህል ቁልፍ ቦታ ነበረው፡፡ ቋንቋን ማስተማር ማለት ሰዋስውን ከማስተማር ተለይቶ አይታይም ነበር፡፡ ሰዋስውም እንደ ይዘት፣ሥርዓተ ትምህርትንና የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት እንደ ማደራጃ መርህ (Organizing Principles) ያገለግል ነበር፡፡ ቋንቋ ማለት የሰዋስው ህጎችን የያዘ በመሆኑ ተማሪዎች ቋንቋውን ለማወቅ እነዚህን ህጎች ማወቅ በቂ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር (Ellis፣2002፣145፤Nassaji and Fotos፣2011፣2)፡፡ Egyankosh(ቀ.የ.) እንዳቀረቡት ግን ሰዋስው በቋንቋ ማስተማር ውስጥ ጉልህ ድርሻ አለው፡ ፡ ይሁን እንጅ “መኪና መንዳት ከፈለግህ የግድ የመኪናውን ውስጣዊ ክፍል፣ እያንዳንዱን ማወቅ የለብህም፤ሁሉንም ማወቅ ሳይጠበቅብህ መኪናህን መንዳት ትችላለህ” በማለት ግልፅ የሆነ ስለ ሰዋስው እውቀት ሳይኖረን መናገር ወይም መፃፍ እንደምንችል ይገልፃሉ፡፡ ባዬ (2000፣xxv) ደግሞ ከሹፍርና ስራ ጋር በማነፃፀር የቋንቋን ሥርዓትና አጠቃቀም ያወቀ ተማሪ ከተራ ሹፌር እንደሚለይና እንዲያውም እንደ መካኒክ ሹፌር እንደሚቆጠር ይገልፃሉ፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ምሁራን ዘንድ በሰዋስው አስፈላጊነት ላይ የሚስማሙ ቢሆንም የትኩረት ልዩነት ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው Klapper and Coleman (2005፣8) “በቋንቋ ማስተማር ውስጥ የሰዋስው ትምህርት በጣም አከራካሪ ጉዳይ ነው” በማለት የሚገልፁት፡፡

የሰዋስውን ትምህርት ወደ ጥንታዊግሪክና ላቲን ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት ሰዋስው ማለት በፍልስፍና፣ በሳይንስ፣ በህግ፣ በሥነመለኮት (Theology) እና በህክምና የትምህርት ዘርፎች ውስጥ የሚያገለግል፣ ተጠየቅን (Logic)፣ ድስኩርን (Rhetoric) ሁሉ አቅፎ የያዘ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ጥሩ ፅህፈት ማለትም ከስህተት ነፃ (Error-Free) የሆነና ትክክለኛነት ላይ ያተኮረ ተደርጎ ይታሰብ ነበር (Patterson፣1999፤Nassaji and Fotos፣2011፣2)፡፡ Lock (1996፣266-267) እንደሚሉት በ1950ዎች፣ 60ዎችና 70ዎች በተዘጋጁት መፃህፍት ውስጥ የነበረው የሰዋስው ትምህርት መዋቅራዊ ብቻ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ለአውድ

የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነበር። ይኸውም ተማሪዎች የቋንቋ ቅርፆች የያዟቸውን ፍቺዎች ሳይረዱ መልመጃዎችን ይሰሩ ነበር። ሰዋስውን በማስተማር ላይ ትኩረት ያደረገው ዘዴ ግን የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ፍላጎት ማሳካት አልቻለም። እናም ይህ ድክመቱ እና ቋንቋን ማወቅ ሰዋስውን ከማወቅ ይበልጣል:: ይኸውም ቋንቋን ማወቅ ማለት ሰዋስዋዊ ዓረፍተ ነገሮችን በትክክል ማፍለቅ ብቻ አይደለም፤በተገቢ ሁኔታ መጠቀም ጭምር እንጅ የሚሉት ሀሳቦች ከሰዋስው -ተኮር ወደ ፍች- ተኮር እንቅስቃሴ እንዲደረግ ምክንያት መሆናቸውን Nassaji and Fotos (2011፣4-9) Long (1991) እና Ellis (1994)ን በመጥቀስ ይገልፃሉ።

ከዚህ በኋላ ግን የሰዋስው ደረጃ (Status) በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ አጠራጣሪ ሆነ። ይኸውም የተወሰኑ የሥነልሳን ባለሙያዎች ለምሳሌ እንደ ቾምስኪ ያሉ የአፊ-ፊት ስልተ-ትወራ አራማጆች ለቋንቋ ለመዳ የበለጠ አስተዋፅኦ የሚያደርገው አለማቀፋዊ ሰዋስው (Universal Grammar) እንጅ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ (Negative Evidence) ጠቀሜታ የለውም አሉ (Bygate et al.፣1994፣3)። መደበኛ የሰዋስው ትምህርትም ለእውቀት ለመዳ (Acquired Knowledge) የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የለውም። ይኸውም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ትክክለኛ ተጨባጭ ግብዓት በዝቅተኛ የማጣራት ሂደት ፍቺ ላይ ትኩረት በማድረግ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ይለምዱታል (Krashen፣1982፣18)። "በጥንቃቄ የተደራጁ መዋቅሮችን መለማመድ ኢቀጥተኛ የሆነ እውቀትን (Implicit Knowledge) ለመልመድ አያስችልም" (Klapper & Coleman፣2005፣74) እና "ሰዋስውን ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ ማስተማር ሳይሆን ተማሪዎች ፍቺ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ ተግባቦታዊ ተግባራት ውስጥ ሲገቡ (Immersed) ቋንቋን የተሻለ ይለምዳሉ" (Nunan፣ 1991፣148-153) የሚሉት ንድፈ ሀሳቦች የሰዋስውን ትምህርት አጣብቂኝ ውስጥ ከተቱት። ከዚህ በተጨማሪ በ1950 ዎች እና በ1960 ዎች የሥነልሳን ባለሙያዎች ጥሩ በሚባለው የሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴ ላይ እርስ በእርስ ባለመስማማታቸው እና የውስጣዊ ብቃት (Langue) ምንነት ለቋንቋ መምህራን መግለፅ ባለመቻላቸው፣ በሌላ በኩል ጥንታዊ ሰዋስው ኢ-ሳይንሳዊ ነው ተብሎ መታሰቡ የቋንቋ መምህራንን ግራ አጋባቸው። እናም ሰዋስውን ማስተማር አያስፈልግም የሚለው በትምህርትቤቶች መስፋፋት ጀመረ (Bygate et al. ፣ 1994 ፣4)።

ይሁን እንጅ አሁን አሁን ሰዋስውን ማስተማር አያስፈልግም የሚለው አመለካከት ከባድ የሆነ ፈተና እየገጠመው መሆኑን ይጠቁማሉ (Nunan፣1989፣13፤Bygate et al.፣1994፣7)። በክፍል ውስጥ በሚሰጠው ተግባር (Task)፣ ቅርፅ (Form) ላይ ማተኮር ዋጋ አለው የሚለው በስፋት ተቀባይነት እያገኘ ከመሆኑም በተጨማሪ ቋንቋውን ለተግባቦት ለመጠቀም ሰዋስው አስፈላጊ የሆነ ሀብት (Resource) መሆኑን ይገልፃሉ (Nunan፣1989 ፣13፤ Bygate et al.፣1994፣7)። Lock (1996፣265-266) በበኩላቸው "አሁን ሰዋስውን ለማስተማር ተሀድሶ (revival) ላይ ነን። ሰዋስው በተግባቦት ላይ ሊጨመር ወይም ሊቀነስ የሚችል አማራጭ ሳይሆን ዋና የደም ስር ነው (Grammar is not an Optional Add-on to Commnication. It lies at the very Heart of Communication.)" በማለት ይገልፁታል።

Patterson (1999) Atwell (1987)ንና Meyer (1990)ን በመጥቀስ የሰዋስው ትምህርት ከተማሪዎች የፅህፈት ትምህርት ጋር ተቀናጅቶ የሚቀርብ ከሆነ ውጤታማ መሆኑን ይገልፃሉ:: Weaver (1996)ን አብነት በማድረግ ደግሞ ሰዋስውን ለማስተማር ገና በቂ ጊዜ እንዳልተሰጠው፣ መደበኛ የሰዋስው ትምህርትም ከተማሪዎች ፅህፈት መነጠል እንደሌለበት ያብራራሉ። Hudson(2001) በበኩላቸው እንደሚያስረዱት የሰዋስው ትምህርት ፔንዱለም በተለይም በእንግሊዝና በአሜሪካ እየተመለሰ ነው። ለምሳሌ በአሜሪካ ግልፅ በሆነ መንገድ ሰዋስውን ማስተማር ያለውን ጠቀሜታ በመያዝ በተለይም በድርሰት ትምህርት እንዲካተት እያደረጉት መሆኑን፣ በእንግሊዝም አዲስ በተመሰረተው ብሄራዊ የማንበብና መፃፍ እቅድ (National Literacy Strategy) እና በብሄራዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት (National Curriculum for English) ውስጥ ሰዋስው አንድ ዋና ምሰሶ (Pillar) ተደርጎ መወሰዱን ይገልፃሉ። ነገር ግን ከቀደምት ጥናቶች ማለትም የሰዋስው ትምህርት በፅህፈት ላይ ተፅዕኖ የለውም፤ አባባል (Myth) እንጅ የሚለውን ከሚያምኑ ወገኖች ተቃውሞ እየገጠመው ቢሆንም በእንግሊዝ ባሉ የመንግስት አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ እየተተገበረ መሆኑን ይገልፃሉ።

Nassaji and Fotos (2011፣137) በበኩላቸው "የሰዋስው እውቀትከመፃፍ ክሂል ተለይቶ አይታይም፤የሁለተኛ ቋንቋ ፅህፈትም ቀጥተኛ የሆነ የሰዋስው እውቀትን የያዘ ነው" በማለት ይገልፃሉ። ከዚህ በተጨማሪ Brown (2000፣362) "የሰዋስው እውቀት

አያስፈልግም ብሎ የሚናገር፣ተግባቦት እንዲሳካ ሰዋስው ቀዳሚ መሆኑን የሚጠራጠር አንድም የለም" በማለት ሲገልፁ Nassaji and Fotos (2011፣1) እና Ellis (2006፣96) በበኩላቸው "የሰዋስው እውቀት ለቋንቋ ማስተማር መሰረታዊ ነገር ነው። ያለ ሰዋስው ቋንቋ መኖር አይችልም"ይላሉ። እናም አንድ የህንፃ ባለሙያ ንድፉን (Blue Print) ተጠቅሞ ማራኪና ቆንጆ ህንፃ እንደሚገነባ ሁሉ አንድ ፀሀፊም ቃላትን ተጠቅሞ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ ፅሁፍ መፍጠር አለበት። መሀንዲሱ የፊዚክስን ህግ መረዳት እንዳለበት ሁሉ ፀሀፊውም የቋንቋውን ህግ እና የቃላትን ባህሪ መረዳት ይኖርበታል (Cook፣ 2010፣97-106)።

ከላይ ከቀረቡት የተለያዩ ምሁራን  ሀሳብ የምንረዳው አንድ ሰው በየትኛውም ደረጃ ላይ ቢሆን የመፃፍ ክሂሉን ለማዳበር የሰዋስው እውቀት ወሳኝ መሆኑን ነው። ከዚህ በመነሳት ለመሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር ምን ይመስላል የሚለውን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አንድ የቋንቋ ተጠቃሚ አንድን ቋንቋ የት፣ እንዴት፣ መቼ፣ ለማን ወዘተ. ነው መጠቀም ያለብኝ የሚለውን ማወቅ ይኖርበታል። በንግግር ጊዜ ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ ቋንቋውን በአካል እንቅስቃሴ መደገፍን በአግባቡ መጠቀም አለበት። የፅህፈት ስራም በአንፃራዊነት ከንግግር የበለጠ ልዩ ጥንቃቄን የሚጠይቅበት አንዱ ምክንያት እነዚህን ምልክታዊ መግባቢያዎች መጠቀም ስለማይቻል ነው። ምሁራን እንደሚሉትም የፅህፈት ስራ በውስጡ ስነልሳናዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ  ጉዳዮችን  ያካተተ ነው። ፅህፈትን በማስተማር ሂደትም  አንዱ ትልቁ ችግር  ክሂሉ  የእነዚህ  የበርካታ የሙያ መስኮች ጥምር የመሆኑ ጉዳይ ነው። በዚህም የተነሳ የፅህፈት ክሂል በርካታ የተወሳሰቡ ችግሮች ያሉበት ነው። ለዚህም ነው ባይረን (1988፣7) ክሂሉ አለማደጉን "ብዙ ተማሪዎች በፅህፈት ዝቅተኛ ችሎታ ያላቸው በመሆኑ አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ ነው" በማለት የሚገልፁት። በመቀጠልም ፅህፈት ምንም እንኳ በርካታ አገልግሎት ቢኖረውም በብዙ ሁኔታ የተረሳ ክሂል መሆኑን ይናገራሉ።ችግሩ በመምህራንም ሆነ በተማሪዎች ላይ በስፋት የሚስተዋል ነው። ለአብነት በክረምቱ መርሃ ግብር ወደ ዩኒቨርሲቲያችን ትምህርታቸውን ለማሻሻል የሚመጡና

የረጅም ጊዜ ቋንቋውን የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን ሳይቀር “በሳል ፅህፈት” የተባለውን ኮርስ ስናስተምር በአማርኛ ቋንቋ ያላቸው የሰዋስው እውቀት አነስተኛ ነው፡፡ በመፃፍ ክሂልላይም በርካታ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን እንደሚፈፅሙ ለማየት ችለናል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ፅህፈት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜያት ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች ውስጥ ለፅህፈት ችሎታ ማነስ ምክንያት ተደርገው የሚቀርቡት በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የፅህፈት መልመጃዎች ብቁ አለመሆን (ሰለሞን ፣1989)፣ የድርሰት ትምህርት ሥርዓት ባለው መንገድ አለመሰጠቱና እርማቱም በተለያዩ ምክንያቶች መቅረቱ (ተስፋዬ ፣1986)፣ የአስተራረም ችሎታ ማነስ (ሰለሞን ፣ 1987)፣ የልምምድ አናሳነት (አለማየሁ ፣1986)፣ የጥንቃቄ ጉድለትና ለስህተት ትኩረት ባለመስጠት መልመድ (አምሳሉና ደምሴ ፣1982) ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በአገር ውስጥ በተደረጉ ጥናቶችም ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ የመጣውን የፅህፈት ክሂል ለማሻሻል መፍትሄ ናቸው ተብለው የቀረቡት ተደጋጋሚ የፅህፈት ልምምድ ማከናወንና ትክክለኛ የሆነ ምጋቤ ምላሽ መስጠት (ሰለሞን ተሰማ፣1987)፣ የቡድን ድርሰት አፃፃፍ ዘዴን መተግበር (ማረው አለሙ፣1987)፣ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ማስተማር (ስዩም ከበደ፣ 1988)፣ስህተቶችን በዓይነት በዓይታቸው በመመደብ የችግሩን ምንጭ መለየት (አለማየሁ ፀጋዬ፣1986) ወዘተ ይገኙበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከመፃፍ ክሂል ጋር በተያያዘ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበርየሚል ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያለው ጥናት አላገኘንም፡፡ ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መንገድም ሀረገወይን በ 2008 ዓ/ም "ተግባቦታዊ ሰዋስውን በፅህፈት አውድ ማስተማር በተማሪዎች ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ላይ ያለው ተፅዕኖ" በሚል ርዕስ በውጭ ቋንቋ ማስተማር፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ካካሄዱት የዶክተሬት ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ ውጭ የተጠና ጥናት የለም፡፡በመሆኑም ይህ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት የሚከተሉትንመሰረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?
2. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው አተገባበር ምን ይመስላል?

3. በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ባላቸው ግንዛቤና አተገባበር መካከል ያለው ዝምድናምን ይመስላል? የሚሉት ይገኙበታል፡፡

### 1.3. የጥናቱዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር መመርመር ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

1. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር፣
2. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውንአተገባበርመፈተሽ፣
3. በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ባላቸው ግንዛቤና አተገባበር መካከል ያለውን ዝምድና ማሳየት ናቸው፡፡

### 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

የመፃፍ ክሂል ብሎም የሰዋስው እውቀት በአንድ ቀን የሚዳብር ስላልሆነ፣ በችግሮች ዙሪያ በየጊዜው መወያየት፣ መነጋገር፣ ምርምር ማካሄድ፣ አጫጭር ሴሚናሮችን ማቅረብ ወዘተ. ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም፣ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

1ኛ. ለመምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ ይጠቁማል፡

2ኛ. ለመምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን አተገባበር በተመለከተ መረጃ ይሰጣል፡፡

3ኛ. ለመርሃትምህርት ቀራጮች፣ ለመፅሃፍ አዘጋጆች፣ ባጠቃላይ ለትምህርት ባለሙያዎች ስነትምህርታዊ እገዛ ያደርጋል፡፡

4ኛ. ከዚህ ጥናት ርዕሰጉዳይ ጋር በተያያዘ፣ በመስኩ ለሚደረጉ ምርምሮች መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

### 1.5. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳውየዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር መመርመር ነው፡፡ ትኩረቱም አማርኛን እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ ዘጠነኛ ክፍል በሚያስተምሩና በእጣ ንሞና በተመረጡ ስድስት ትምህርት ቤቶች በሚገኙ መምህራን ላይ ብቻ ተወስኗል፡፡ ከይዘት አንፃርም

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር ማሳየት እና በመምህራን የሰዋስው እርማት ግንዛቤና አተገባበር መካከልያለውንዝምድና መመርመር ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት የታሰበውን ዓላማ ለማሳካት መረጃዎችን በመጠናዊና በዓይነታዊ ዘዴ ለመሰብሰብ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በኮረና ምክንያት ዓይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሆነውን የቡድን ተኮር ውይይት መጠቀም አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ዓላማዎች የተመለሱት በመጠናዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ብቻ በመሆኑ ከሶስት ማዕዘናዊነት (Triangulation) አንፃር ይህ ጥናት የራሱ የሆነ ውስንነት ይኖረዋል፡፡

## 1.7. የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም ሙያዊ ብያኔ

**የሰዋስዋዊ እውቀት (Grammatical Knowledge)፡-** መደበኛ ትክክለኛ ዓ/ነገር የማፍለቅ ወይም የመረዳት ችሎታን የሚያመለክት እውቀት ነው፡፡ይህም የቃላትን፣ የሥነ አገባብን፣የሥነድምፅና የጽሁፍ እውቀትን ያመለክታል::

**የሰዋስው እርማት፡-**ከሥነድምፅ ጀምሮ እስከ ሥነ አገባብ ድረስ ያሉት ሁሉም ሰዋስዋዊ ስህተቶች ከትክክለኛነት (Accuracy) እና ከቅቡልነት (Acceptability) አንፃር የሚደረግን እርማት ይመለከታል፡፡

**የሰዋስው እርማት ግንዛቤ**፡-ቀጥተኛውንም ሆነ ኢ-ቀጥተኛውን ዘዴ ለመጠቀም ከመወሰናችን በፊት የተማሪዎችን ደረጃ፣ የስህተቱን ዓይነት፣ ተማሪዎች ቋንቋውን የለመዱበትን ሁኔታ ወዘተ. ከግምት ውስጥ ማስገባትን የሚመለከት ነው፡፡

**የሰዋስው እርማት አተገባበር፡-** እንደተማሪዎችን ደረጃ፣ እንደስህተቱ ዓይነት፣ ተማሪዎች ቋንቋውን እንደለመዱበት ሁኔታ ወዘተ. ቀጥተኛውን ወይም ኢ-ቀጥተኛውን ዘዴ በመጠቀም የሚደረግን የእርማት አሰጣጥ ይመለከታል፡፡

**ቀጥተኛ ዘዴ፡-** ቀጥተኛ በሆነው ምጋቤ ምላሽ ተማሪው የተናገረው፣ የፃፈው ስህተት የነበረ መሆኑን በመግለፅ ትክክለኛውን ቅርፅ ብቻ በመጠቆም ወይም ከሥነ-ልሳናዊ

ማብራሪያ (Meta Linguistic Information) ጋር በመስጠት የሚቀርብበት ዘዴ ነው (Ellis et al., 2009፡ 304)፡፡

**ኢ-ቀጥተኛ ዘዴ፡-** በኢ-ቀጥተኛ ምጋቤ ምላሽ ጊዜ ግን ግልፅ የሆነ ስህተቱን የሚጠቁም መረጃ የለም፡፡የስህተት ምልክቶችን መጠቀም /ለምሳሌ፡-VT (Verb Tense Error) ወዘተ. በማለት የስህተቱን ዓይነት በአጭሩ የሚገለፅበት ወይምስህተቱ ይጠቆማል፤የት ላይ ስህተት እንደሆነ አይገለፅም፡፡ ለምሳሌ ስህተቱ ከሚገኝበት መስመር ጠርዝ ላይ (X) ምልክት ማድረግ፣ ስህተቱ በሚገኝበት ቦታ ላይ በማስመር መጠቆም ወዘተ. ይመለከታል፡፡

## 2.የምርምሩ ስነዘዴ

### 2.1. የምርምሩ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመፃፍ ክሂል ላይ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤከአተገባበራቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓላማም ለማሳካትም ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍ (Correlational design) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

## 2.2 የትምህርት ቤትና የመምህራን ናሙና አመራረጥ

### 2.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የምስራቅ ጎጃም ዞን የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ባለሙያ በሰጡት መረጃ መሰረት በምስራቅ ጎጃም ዞን 64ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች መካከል በእጣ ንሞና ስልት ስድስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (አምበር፣ሉማሜ፣የትኖራ፣ ደጀን፣ ደ/ወርቅና መርጦለማርያም) ተመርጠዋል፡፡ የእጣ ንሞና ስልት የተመረጠበት ምክንያትበዞኑ ለሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እኩል እድል ስለሚሰጥና የጥናቱን ውጤት በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለማጠቃለል ስለሚያስችል ነው፡፡ ስድስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ የሚጠናው ክሂል የመፃፍ ክሂል ስለሆነ፣ከእነዚህ በላይ ትምህርት ቤቶችን መርጦ ማጥናት አስፈላጊነቱ ባይካድም በየትምህርት ቤቱ የሚገኙትን መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር በተለያዩ ትምህርት ቤቶች

በፅሁፍ መጠይቅና በምልከታ ማረጋገጥ ግን ጊዜ የሚፈልግ በመሆኑ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙት የክፍል ደረጃዎች መካከል ደግሞ ዘጠነኛ ክፍልሲመረጥየሚከተሉትን ምክንያቶች ታሳቢበማድረግ ነው፡፡

አንደኛ ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ክልል አቀፍ በሆነው የመማሪያ መፅሀፍ ሲማሩ ከቆዩ በኂላ ከአንደኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ የሚሸጋገሩበት በመሆኑተመሳሳይ የመፃፍ ክሂል ችሎታ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታሰብበት የክፍል ደረጃ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት መምህራንስ በዚህ የክፍል ደረጃ ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር ምን ያህል ተመሳሳይ ነው የሚለውን ለማወቅ ስለሚያስችል ነው፡፡

ሁለተኛ ዘጠነኛክፍልከዚህ በኂላ ለሚቀጥሉት የክፍል ደረጃዎች ማለትም ተማሪዎች ወደፊት ለሚኖራቸው የመፃፍ ችሎታ መሰረት የሚጥሉበት ወሳኝ የክፍል ደረጃበመሆኑ በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ ለሚታዩ ችግሮች ምንጭ የሆኑ ተላውጦዎችን (በዋናነት መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር በተመለከተ) ከወዲሁ አውቆ መፍትሄ መፈለግ ስለሚያስችል በታላሚ ንሞና ተመርጧል፡፡

### 2.2.2. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የምስራቅ ጎጃም ዞን የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ባለሙያ በሰጡት መረጃ መሰረት በምስራቅ ጎጃም ዞን 64 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ጥናቱ በዋናነት ተዛምዷዊ ከሆነ የተጠኝዎች ቁጥር Cohen (2000፣93) እንደሚሉት ከ 30 ማነስ የለበትም:: በመሆኑም በስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች 9ኛ ክፍል አማርኛ የሚያስተምሩ 37 መምህራንበጥቅል ንሞና ዘዴተመርጠዋል፡፡

## 2.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፅሁፍ መጠይቅና ምልከታናቸው፡፡

### 2.3.1 የመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ

የዚህ ጥናት የፅሁፍ መጠይቅ ዋና ዓላማ 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ዓላማ ታሳቢያደረጉ

ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎቹም ዝግ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን በሊከርት ወይም በሬቲንግ ስኬል መልክ ቀርበዋል፡፡

የፅሁፍ መጠይቁ ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን፣ በክፍል አንድ አጠቃላይ የመምህራን መረጃ (ማለትም የትምህርት ደረጃ፣ እድሜ፣ ፆታ፣ ወዘተ.)የቀረቡ ሲሆን በክፍል ሁለት ደግሞ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ማለትም የሰዋስው እርማት አሰጣጥ ዘዴዎችን በተመለከተ በአዎንታዊና በአሉታዊ መንገድ ቀርበዋል፡፡ ሁለቱም የቀረቡት በባለ አምስት ሊከርት ስኬል ሲሆን በቅደም ተከተል በጣም እስማማለሁ (5)፣ እስማማለሁ (4)፣ በመጠኑ እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም (2)፣ በጣም አልስማማም (1) ነጥብ እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም የተለያዩ ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ከተደረገ በኋላ ቅድመ ጥናት (pilot study) በሌሎች ትምህርትቤቶች ማለትም በጥናቱ በማይሳተፉ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ሙከራ ተደርጓል፡፡ በዚህም የፅሁፍ መጠይቁ ውስጣዊ አስተማማኝነት በክሮንባች አልፋ ተለክቶ 0.78 ሆኖ በመገኘቱ ለዋናው ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን አገልግሏል፡፡

### 2.3.2. ምልከታ

ምልከታው በስድስት ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ የተካሄደ ነው፡፡ ይኸውም ከእያንዳንዱ ትምህርትቤት 9ኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር ልክ አንድ አንድ ክፍል በእጣ ተመርጧል፡፡ምልከታያስፈለገበት ዋናው ምክንያት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት ጊዜ የሰዋስውን እርማት እንዴት እንደሚሰጡ ለማወቅ ስለሚያስችል ነው፡፡ ይኸውም የተለያዩ ምሁራን በምዕራፍ ሁለት የሰጡትን ንድፈ ሃሳባዊ ገለፃና ማብራሪያ መነሻ በማድረግ በአጥኚዎችየምልከታ ዝርዝሩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ከዚያም የተለያዩ ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ከተደረገ በኋላ ቅድመ ጥናት (pilot study) በሌሎች ትምህርትቤቶች ማለትም በጥናቱ በማይሳተፉ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ሙከራ ከተደረገ እና ግልፅነት የሌላቸው ጥያቄዎች ማስተካከያ ከተደረገባቸው በኋላ ለዋናው ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን አገልግሏል፡፡ ለምልከታ የተዘጋጁ ጥያቄዎችም ዝግ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

## 2.4. የመረጃ መተንተኛ ስልቶች

በዚህ ጥናትከፅሁፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች በአሃዛዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ ይኸውም መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ በፅሁፍ መጠይቅ አተገባበራቸውን ደግሞ በምልከታ ተሰብስቧል፤ በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በዓይነት በዓይነት ከተደራጀ በኋላ በነጠላ ናሙና ቲ ቴስት ተተንትኗል፡፡ ከምልከታ የተገኘውን መረጃ በተመለከተም የሁለቱ ተመልካቾች (አጥኝዎች) አማካይ ውጤት ተወስዶ ለትንተና አገልግሎትውሏል፡፡ ከምልከታየተገኘውም መረጃ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ ይኸውም ከጥናቱ መረጃ የተገኘው አማካይ ውጤት (Mean) ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected Mean) በላይ ወይም በታች መሆኑን በማየትና በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት በመፈተሽ ግንዛቤያቸውም ሆነ አተገባበራቸው ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚያም በመምህራን የሰዋስው እርማት ግንዛቤና በአተገባበራቸው መካከል የሚኖረው ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ዘዴ ተረጋግጧል፡፡

### 2.5. ሥነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች

የጥናቱ ተሳታፊዎች ለምርምሩ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በነፃነት መስጠት እንዲችሉ የምርምር ሥነ-ምግባር መከበር አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አጥኝዎችጥናቱን ለማካሄድ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት የትብብር ደብዳቤ ከማፃፍ ጀምሮ ከመረጃ ሰጭ አካላት (መምህራን) ጋር ስለ ምርምሩ ምንነትና ዓላማ ውይይት በማድረግ በምርምር ስራው በቅንነት እንዲሳተፉና መረጃ የመስጠት ሂደቱም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህ ጊዜ ለምርምሩ የሚሰጡት መረጃ ከጥናቱ ዓላማ ውጭ እንደማይውልና የመረጃ ሰጭዎች ማንነትም ለማንም እንደማይገለፅ ተነግሯቸዋል፡፡ ባጠቃላይ የአሜሪካ የሥነ-ልቦና ማህበር በ2017 ያወጣው የምርምር ሥነ-ምግባር በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 3. የመረጃዎች ትንተናና ማብራሪያ

### 3.1. የመረጃዎች ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር መፈተሽ ነበር፡፡ በዚህ መሰረት መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ በፅሁፍ መጠይቅ አተገባበራቸውን ደግሞ በምልከታ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡

፡ ከዚህ በመቀጠል በመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

### 3.1.1.የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል

መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ በነጠላ ናሙና ቲ ቴስት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ሰንጠረዥ 3.1 የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ የሚያሳይ የነጠላ ናሙና ውጤት

| | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | መደበኛ አማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| **የሰዋስው እርማት ግንዛቤ (የፅሁፍ መጠይቅ ውጤት)** | 37 | 87.95 | 6.169 | 1.014 |

<table>
<tr><td colspan="7">የነጠላ ናሙና ቲ- ቴስት</td></tr>
<tr><td rowspan="3"></td><td colspan="6">የሚጠበቅ አማካይ = 111</td></tr>
<tr><td rowspan="2">የt ዋጋ</td><td rowspan="2">የነፃነት ደረጃ (df)</td><td rowspan="2">የጉልህነት ደረጃ(ባለ-2 አቅጣጫ)</td><td rowspan="2">የአማካይ ልዩነት (Mean Difference)</td><td colspan="2">95% Confidence Interval of the Difference</td></tr>
<tr><td>ዝቅተኛ</td><td>ከፍተኛ</td></tr>
<tr><td>የፅሁፍ መጠይቅ ውጤት</td><td>-22.733</td><td>36</td><td>.000</td><td>-23.054</td><td>-25.11</td><td>-21.00</td></tr>
</table>

ከላይ ከሰንጠረዥ-3.1 እንደምንመለከተው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ በአማካይ 87.95 ሲሆን ከሚጠበቀው አማካይ (111) በ 23.054 ያነሰ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ግንዛቤያቸው ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ልዩነት ግን ጉልህ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ማየት ስለሚያስፈልግ ከላይ እንደቀረበው በ 36 (df) የናሙና ብዛት በባለ ሁለት አቅጣጫ ፍተሻ (t=22.733, df=36, $p<0.05$) ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛና በመካከላቸውም ጉልህ የሆነ የግንዛቤ ልዩነት ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስውን እርማት እንዴት እንደሚተገብሩት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 3.1.2. የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው እርማት አተገባበር ምን ይመስላል

**ሰንጠረዥ-3.2የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን አተገባበር ሚያሳይ የነጠላ ናሙና ውጤት**

| | የናሙና ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | መደበኛ አማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| አተገባበር (የምልከታ ውጤት) | 37 | 73.76 | 5.294 | .870 |

| የነጠላ ናሙና ቲ- ቴስት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሚጠበቅ አማካይ = 111 | | | | | |
| | የt ዋጋ | የነፃነት ደረጃ (df) | የጉልህነት ደረጃ(ባለ-2 አቅጣጫ) | የአማካይ ልዩነት (Mean Difference) | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| አጠቃላይ የምልከታ ውጤት | -42.795 | 36 | .000 | -37.243 | -39.01 | -35.48 |

ከሰንጠረዥ-3.2 እንደምንመለከተው መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው አተገባበር በአማካይ 73.76 ሲሆን ከሚጠበቀው አማካይ (111) በ 37.243 ያነሰ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የመምህራን የሰዋስው እርማት አተገባበር ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ የአማካይ ልዩነት ግን ጉልህ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በ 36 (df) የናሙና ብዛት፣ በባለ ሁለት አቅጣጫ (t=42.795,df=36, P<0.05) ጉልህ ልዩነት ያሳየ መሆኑን የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመነሳት የመምህራን የሰዋስው እርማት አተገባበር ዝቅተኛና በመካከላቸውም ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን መናገር ይቻላል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በመምህራን የሰዋስው እርማት ግንዛቤና አተገባበር መካከል ያለውን ዝምድና ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 3.1.3. በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስውን እርማትና አተገባበር መካከል ያለው ዝምድና ምን ይመስላል

ሰንጠረዥ-3.3 የመምህራንን የሰዋስው እርማት ግንዛቤና አተገባበር ዝምድና የሚያሳይ

| ተዛምዶ | | የሰዋስው እርማት ግንዛቤ | የሰዋስው እርማት አተገባበር |
|---|---|---|---|
| የሰዋስው | የፒርሰን ተዛምዶ | 1 | .000 |
| እርማት | ጉልህነት (ባለ 2 አቅጣጫ) | | .998 |
| ግንዛቤ | ናሙና (N) | 37 | 37 |
| የሰዋስው | የፒርሰን ተዛምዶ | .000 | 1 |
| እርማት | ጉልህነት (ባለ 2 አቅጣጫ) | .998 | |
| አተገባበር | ናሙና (N) | 37 | 37 |

ከሰንጠረዥ-3.3 እንደምንመለከተው በመምህራን የሰዋስው እርማት ግንዛቤና አተገባበር መካከል ያለውን ዝምድና በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ዘዴ ተፈትሾ ጠንካራ ተዛምዶ (r=0.998) እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሁለቱ ዝምድና ጉልህ (p<0.001) ሲሆን ከአቅጣጫ አንፃር አዎንታዊ ነው፡፡ ይህም መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ሲጨምር አተገባበራቸው የሚጨምር ሲሆን በተቃራኒው ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ሲቀንስ አተገባበራቸው የሚቀንስ መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 3.2. የጥናቱ ማብራሪያ

ይህ ጥናት በዋናነት የሚያተኩረው በመፃፍ ክሂል ላይ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር ማሳየት ነበር፡፡ በመሆኑም ለዚህ ዓላማ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በፅሁፍ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ ከተሰበሰቡ በኋላ በነጠላ ናሙና ቲ ቴስት ተተንትነው የተገኙት ውጤቶች (ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር) ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይኸውም መምህራን የሰዋስው እርማት መስጠትን አስፈላጊነት የተገነዘቡ ቢሆንም የመጀመሪያውን የተማሪዎችን ረቂቅ ፅሁፍ በሚያርሙበት ጊዜ ቅድሚያ ለሰዋስው ትኩረት መስጠታቸው ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ የመጨረሻውን የተማሪዎችን ፅሁፍ በሚያርሙበት ጊዜ ቅድሚያ ለይዘት ትኩረት የሚሰጡ መሆኑFerris (2003) ከሚያነሱት ሀሳብ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ይኸውም Ferris (2003) እንደሚሉት በፅህፈት ላይ የሚሰጥ ምጋቤ ምላሽን በተመለከተ መምህራን በመጀመሪያ ደረጃ ፍቺ እና ይዘት ላይ ማተኮር አለባቸው፤ በቅርፅ ላይ የሚሰጠውን ምጋቤ ምላሽ ደግሞ መጨረሻ ላይ ማድረግ ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ ምክንያቱም አስቀድሞ በቅርፅ ላይ ትኩረት ማድረግ ለይዘት እንቅፋት ይሆናል ይላሉ፡፡

የሰዋስውን እርማት ከምንሰጥባቸው ዘዴዎች አንፃርም መምህራን አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት ቀጥተኛውን ዘዴ ነው፡፡ ቀጥተኛውዘዴ ደግሞ በዋናነት በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ላይ የሚተገበር ነው፡፡ Hyland (2003፣181) እንደሚሉት ቀጥተኛ የሆነ እርማት ከማድረግ ይልቅ ስህተት የሚገኝበትን ቦታ መጠቆም፣የስህተት ዓይነቱን መግለፅ፣ የበለጠ ተማሪዎችን ያነቃቃቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተማሪዎችን በራስ የማረም ስልትም ያዳብራል፡፡ Sheen (2007፣255) በበኩላቸው Ferris(2002)ን በመጥቀስ እንደሚሉት ከሁለተኛ ቋንቋ ፅህፈት ሥነ-ትምህርት አንፃር ለተማሪዎች ከቀጥተኛ እርማት ይልቅ ኢ-ቀጥተኛ የሆነው እርማት የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም ኢ-ቀጥተኛ እርማት ተማሪዎችን በመላምት ሙከራ (Hypothesis Testing) ውስጥ እንዲገቡና ጥልቅ የሆነ አእምሯዊ ተግባራትን በማከናወን ትክክለኛውን ቅርፅ እንዲለምዱ ይገፋፋል ይላሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የዚህ ጥናት ውጤት Hyland (2003) እና Sheen (2007) ካነሱት ሃሳብ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት በተገኘው ውጤት መሰረት መምህራን ሁሉንም ሰዋስዋዊ ስህተት መታረም አለበት የሚል ግንዛቤ ያላቸውና ይህንኑ የሚተገብሩ ናቸው፡፡ ይህም Richards and Renandya (2002፣304-333)፣ Raimes (1983፣151) እና Ferris and Hedgcock (2005፣ 264) ካቀረቡት ሃሳብ ጋር የሚጣረስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም እነዚህ ምሁራን በእርማት ጊዜ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚስተዋሉ ስህተቶችን ሙሉ በሙሉ ከማረም ይልቅ ለተግባቦት እንቅፋት ናቸው በሚባሉ አብይ ስህተቶች (Global Error) ላይ ትኩረት ማድረግ ተመራጭ ነው በማለት የእርማት ስራ ትኩረት ማድረግ ያለበት በጣም ተደጋጋሚ በሆኑ ስህተቶች በተለይም አብይ ፍቺ (Global meaning) በሚያደናቅፉ ስህተቶች ላይ ብቻ መሆን አለበት በማለት ይገልፃሉና፡፡

ባጠቃላይ የመምህራን የሰዋስው እርማትና አተገባበር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ገነት በ 2009 ዓ/ም “የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ትምህርት አተገባበርና ግንዛቤ ፍተሻ(በምስራቅ ጎህ፣ በሽመልስ ሀብቴና በጠመንጃ ያዥ ሁለተኛ ደረጃትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችና መምህራንተተኳሪነት)” በሚል በአዲስ አበባ መስተዳድር ካጠኑትየጥናቱ ውጤት ማለትም ”የሰዋስው የትምህርት አተገባበርና ግንዛቤ መርህ ያልተከተለ መሆኑ ታውቋል” ከሚለውጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 4 ማጠቃለያና ምክረ-ሃሳብ

### 4.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር መፈተሽ ነበር፡፡ በዚህ መሰረት መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ በፅሁፍ መጠይቅ አተገባበራቸውን ደግሞ በምልከታለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በነጠላ ናሙና ቲቴስት ተተንትነው የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ዓላማ በተመለከተ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ በአማካይ 87.95 ሲሆን ከሚጠበቀው አማካይ (111) በ 23.054 ያነሰ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ግንዛቤያቸው ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ውጤት ማለትም መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ  በባለ ሁለት አቅጣጫ ፍተሻ ($t=22.733$, $df=36$, $p<0.05$) ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛና በመካከላቸውም ጉልህ የሆነ የግንዛቤ ልዩነት ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የዚህ ጥናት ሁለተኛው ዓላማ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸውን አተገባበር የሚመለከት ሲሆን የተገኘው ውጤትም በአማካይ 73.76 ሲሆን ከሚጠበቀው አማካይ (111) በ37.243 ያነሰ ነው፡፡ በመሆኑም የመምህራን የሰዋስው እርማት አተገባበር ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ በመምህራን መካከል ያለው የአተገባበር ልዩነትም በባለ ሁለት አቅጣጫ ተፈትሾ ($t=42.795$, $df=36$, $P<0.05$) ጉልህ ልዩነት ያሳየ መሆኑን የተገኘው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም የጥናቱን ሶስተኛ ዓላማ በተመለከተ በመምህራን የሰዋስው እርማት ግንዛቤና አተገባበር መካከል ያለውን ዝምድና በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ዘዴ ተፈትሾ ጠንካራ ተዛምዶ ($r=0.998$) እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሁለቱ ዝምድና ጉልህ ($p<0.001$) ሲሆን ከአቅጣጫ አንፃር አዎንታዊ ነው፡፡ ይህም መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ሲጨምር አተገባበራቸው የሚጨምር ሲሆን በተቃራኒው ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤ ሲቀንስ

አተገባበራቸው የሚቀንስ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ከእነዚህ ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉትን ምክረ-ሃሳቦች ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

## 4.2 ምክረ-ሃሳብ

ከዚህ ጥናት በተገኘው ውጤት መሰረት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ሰዋስው እርማት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በመሆኑም፡-

አንደኛ የትምህርት ባለሙያዎች በተለይም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው እርማት እንዴት መስጠት እንዳለባቸው ስልጠና ቢሰጡ፣

ሁለተኛ የመፅሀፍ አዘጋጆች ወደፊት ከመፃፍ ክሂል መልመጃዎች ጋር መምህራን የሰዋስውን እርማት እንዴት መስጠት እንዳለባቸው በተለይም በመምህሩ መምሪያ ላይ ማብራሪያ ወይም ጥቆማ ቢሰጡ፣

ሶስተኛ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው እርማት እንዴት መተግበር እንዳለበት ወቅቱ ከሚጠይቀውና ከዘመኑ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ጋር ራሳቸውን በንባብና በስልጠና ማሻሻል ቢችሉ፣

አራተኛ ወደፊት ሌሎች ተመራማሪዎች የሰዋስውን እርማት ከምንሰጥባቸው ዘዴዎች (ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ) መካከል የትኛው ተመራጭ ነው? ለምን? የሚለውን በተመለከተ ተጨማሪ ጥናትና ምርምር ቢያደርጉመልካም ነው እንላለን፡:

## ዋቢፅሁፎች


ማረው ዓለሙ ::( 1987): “በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል በሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ግምገማ::” ለአማርኛ ኤም ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

ሰለሞን ሀለፎም (1989) “አማርኛን በማስተማሪያ ዘዴነት የቃል ፅህፈት (Dictation) ሚና፡፡” ለአማርኛ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

ሰለሞን ተሰማ ፡፡(1987)፡፡ "የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት፡፡" ለአማርኛ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

ስዩም ከበደ ፡፡(1988)፡፡ "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት፡፡" ለአማርኛ ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

ባየ ይማም ፡፡( 1987)፡፡ *የአማርኛ ሰዋሰው፡፡* አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ

------------- ፡፡(2000)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ

ተስፋዬ ሸዋዬ ፡፡(1986)፡፡ *አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር፡፡* አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ

አለማየሁ ፀጋዬ ፡፡(1986)፡፡ "በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና፡፡" ለአማርኛ ኤም ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

አምሳሉ አክሊሉና ደምሴ ማናህሎት ፡፡(1982)፡፡ *ጥሩ የአማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው ?* አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ክፍሌ ሀብተማርያም ፡፡(1986)፡፡ "የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታ፡፡" ለአማርኛ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

ጌታሁን አማረ ፡፡(1990)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡* አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቀ ሙሉ ፡፡(1998)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር (ሁለተኛ እትም)፡፡* ባህር ዳር፡- አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡

Agustin Liach, M. (2011). *Lexical Errors and Accuracy in Foreign Language Writing.* London: MPC Books Group.

Akmajian, A., Demers, R., Farmer, A., & Harnish, R. (2004). *Linguistics: An Introduction to Language and Communication (5th Ed.).* New Delhi: Prentice-Hall of India.

Anker, S. (2004). *Real Writing with Readings: Paragraphs and Essays for College Work and Every Day Life (3rd Ed.).* Boston: Bedford/ST.Martin's.

Ashwell, T. (2000). "Patterns of teacher responseto student writing in a multiple-draft composition: Is Content Feedback followed by Form Feedback the best method?". *Journal of Second Language Writing. 9(3)* , 227-258.

Bachman, L. F. (1989). *Fundamental Considerations in Language Testing.* Hong Kong: OUP.

Bialystock, E. (1978). "A theoretical Model of Second Language Learning". *Language Learning, 28,* , 69-84.

Bitchener, J., Young, S., & Cameron, D. (2005). " The Effect of Different Types of Corrective Feed back on ESL Students Writing." *Journal of Second Language Writing,Vol.14,* , 191-205.

Broughton, G., Brumfit, C., Flavell, R., Pincas, A., & Hill, P. (1978). *Teaching English as a Foreign Language.* London & New York: Routledge.

Brown, D. (1994). *Principles of Language Learning and Teaching.* EngleWood Clifs: Prentice-Hall Regents.

Brown, D. (2000). *Principles of Language Learning and Teaching (4th Ed.).* California: Longman.

Brown, H. (2007). *Principles of Language Learning and Teaching (5th Ed.).* New York: Pearson Education.

Bygate, M., Tonkyn, A., & Williams, E. (1994). *Grammar and the Language Teacher.* London: Prentice-Hall.

Byren, D. (1988). *Teaching Writing Skills.* Hong Kong: Long man Group (FE).

Celce-Murcia, M. (1991). *Teaching English as a Second or Foreign Language.* Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Celce-Murcia, M. & Hilles, S. (1988). *Techniques & Resources in Teaching Grammar.* Oxford: Oxford University Press.

Chandler, J. (2003). " The Efficacy of Various Kinds of Feedback for Improvement in the Accuracy and Fluency of Student Writing". *Journal of Second Language Writing, 12 (3),* 267-296.

Cizek, G., Germuth, A., & Schmid, L. (2011). *A check list for Evaluating Credentialing Testing Programs*. Kalamazoo: The Evaluation Center,Western Michigan University.

Cohen, L., Manion, L., & Morrison, K. (2000). *Research Methods in Education (5th Ed.).* London & New York: Routledge Falmer.

Coleman, J.A., & Klapper, J. (2005). *Effective Learning and Teaching in Modern Languages*. London & New York: Routledge.

Cook, H. (2010). *Academic Language/Literacy Strategies for Adolescents A "How To" Manual for Educators*. New York & London: Routledge.

Corder, S. (1981). *Error Analysis and Interlanguage.* London: Oxford University Press.

Creswell, J. (2009). *Research Design: Quantitative,Qualitative & Mixed Method Approach (3rd Ed.)*. London: Sage Publication Inc.

Dornyei, Z. (2007). *Research Methods in Applied Linguistics: Qualitative,Quantitative & Mixed Methodologies*. Uk:: Oxford University Press.

Ellis, R. (2009). " Corrective Feedback and Teacher Development." *L2 Journal, 1 (1)*,3-18.

Ellis, R. (2006). " Current Issues in the Teaching of Grammar: An SLA Perspective." *TESOL QUARTERLY Vol.40,No.1*.NewZealand: University of Auckland.

Ellis, R. (2002). " Grammar Teaching Practice or Consciousness-Raising?" In Richards, J.C. & Renandya,Willy, A. (Eds.), *Methodology in Language Teaching: An Anthology of Current Practice,* (pp. 167-175). Cambridge: Cambridge University Press.

Ellis, R. (1997). *Second Language Acquisition.* Oxford: Oxford University Press.

Ellis, R. (1999). *The Study of Second Language Acquisition.* Philadelphia: College of Education,Temple University.

Ellis, R., Loewen, S., & Erlam, R. (2009). " Implicit & Explicit Corrective Feedback and the Acquisition of L2 Grammar." In Ellis, R., Loewen, S., Elder, C., Erlam, R., Philp, J., & Reinders, H. *Implicit and Explicit Knowledge in Second Language Learning, Testing and Teaching* (p. 303-334). London: Short Run Press Ltd.

Egyankosh. (n.d.)*" Current Trends in Teaching Grammar"* Retrived From: http://www.egyankosh.ac.in/bitstream/123456789/26468/1/Unit-15.pdf

Fathman, A. K., & Whalley, E. (1990). " Teacher Response to Student Writing: Focus on Form Versus Content." In Kroll, B. *Second Language Writing: Research Insight for the Class Room* (pp. 178-191). Cambridge: Cambridge University Press.

Ferris, D. (1999). "The Case for Grammar Correction in L2 Writing Class: A response to Truscott." *Journal of Second Language Writing,8* , 1-10.

Ferris, D., & Roberts, B. (2001). " Error Feedback in L2 Writing Classes: How Explicit does it need to be?"*Journal of Second Language Writing,10* , 161-184.

Ferris, D. (2002). " Teaching Students to Self Edit." In Richards, J.C. & Renandya,Willy, A. (Eds.), *Methodology in Language Teaching: An Anthology of Current Practice,* (pp. 328-335). Cambridge: Cambridge University Press.

Ferris, D. (2004). " The Grammar Correction Debate in L2 Writing: Where are we, and Where do we go from here? (and what do we do in the mean time...?). *Journal of Second Language Writing* , 49-62.

Ferris, D. (2003). *Response to Student Writing: Implications for Second Language Students*. London: Erlbaum Associates Inc.

Ferris, D., & Hedgcock, J. (2005). *Teaching ESL Composition Purpose,Process and Practice.* USA: Lawrence Erlbaum Associates,Inc.

Gardner, R. C. (May 30,2005). " Integrative Motivation and Second Language Acquisition". *Canadian Association of Applied Linguistics*. *London, Canada.*

Gass, S. (1988). "Second Language Vocabulary Acquisition." *Annual Review of Applied Linguistics,9* , 92-106.

Haregewain, A. (2008). *"The Effect of Communicative Grammar on the Grammatical Accuracy of Students' Academic Writing: An Integrated Approach to TEFL" un Published PHD Thesis*. Addis Ababa: Addis Ababa University.

Harmer, J. (1983). *The Practice of English Language Teaching*. USA: Longman.

Hinkel, E., & Foto, S. (2002). *New Perspectives on Grammar Teaching in Second Language Classrooms*. USA: Lawrence Erlbaum Associates,Inc.

Hudson, R. (2001). *"Grammar Teaching and Writing Skills: The Research Evidence."* London: Department of Phonetics & Linguistics, 17.1-6. Retrived from: 1

Hyland, K., & Ann, E. (2006). " Teachers Perceptions of Error: The Effects of First Language and Experience." *Journal of Science Direct System, 34*, 509-519. London & Japan: Elsevier Ltd.

Kato, A. (2006). " Error Analysis of High School Student Essays". *Accents Asia [on line] 1(2) Avilable* , 1-13. Retrived From: http://www.accentsasia.org/1-2/kato.pdf.

Kroll, B. (1990). " What does time buy? ESL Student Performance on Home Versus Class Compositions". In Kroll, B. *Second Language Writing: Research Insight for the Class Room* (pp. 140-153). Cambridge: Cambridge University Press.

Marczyk, G., Dematteo, D., & Festinger.D. (2005). *Essentials of Research Design and Methodology*. USA: John Wiley & Sons,Inc.

Muijs, D. (2004). *Doing Quantitative Research in Education with SPSS.* London: Sage Publications.

Polio, C. (1997). " Measures of Linguistic Accuracy in Second Language Writing Research." *Language Learning, 47 (1)* , 101-143.

Richards, J. C. (1974). *Error Analysis Perspectives on Second Language Acquisition.* London & New York: Long man.

Richards, J. C., & Renandya,Willy, A. (2002). *Methodology in Language Teaching: An Anthology of Current Practice.* Cambridge: Cambridge University Press.

Schmidt, R. (1990). "The Role of Consciousness in Second Language Learning." *Applied Linguistics, 1 (1)*, 129-158.

Seow, A. (2002). "The Writing Process and Process Writing." In Richards, J.C. & Renandya,Willy, A. (Ed.), *Methodology in Language Teaching: An Anthology of Current Practice* (p. 315-320). Cambridge: Cambridge University Press.

Truscott, J. (1996). " The Case against Grammar Correction in L2 Writing Classes." *Journal of Language Learning, Vol.46, No.2*, 327-369.

Ushida, E. (Sep.2005). *"The Role of Students Attitudes and Motivation in Second Language Learning in online Language Courses", Vol.23, No.1.* Sandiego: University of California. Retrieved from: HYPERLINK "https://calico.org/memberBrowse.php?action=article&id=131" https://calico.org/memberBrowse.php?action=article&id=131 .